# የወላጅ/አሳዳጊ መመሪያ

## የተጠቃን ሰው ከችግሩ እንዲያገግም የመርዳት ሂደት 1973 ደንብ ሰክሽን 504
## Section 504 of the Rehabilitation Act of 1973

### ሰክሽን 504 ምንድነው?

ሰክሽን 504 የማገገሚያ ደንብ 1973 (ሰክሽን 504) ማለት የአካል ስንክልና ያለባቸው ዜጎችን መብት የሚያስጠብቅ የፌደራል ህግ ነው። ህጉ/ደንቡ ማናቸውም ከፌደራል ገንዘብ/ፈንድ/በጀት የሚያገኙ ድርጅቶች በአካል ስንክልና ምክንያት ብቃት ያላቸውን ግለሰቦች አድልዎ እንዳይደረግባቸው ይከለክላል። ጠቅላላ የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ፕሮግራሞች እና እንቅስቃሴዎች በሰክሽን 504 መሰረት ተግባራዊ መደረግ አለባቸው።

የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ MCPS Regulation ACG-RB 1973 ደንብ ሰክሽን 504 በመልሶ ማቋቋም ስለሚታቀፉ ተማሪዎች ያለችግር የሚገለገሉበትን/Accommodations ተገቢ የሆነ ለውጥና-የማሻሻያ ሒደት ለተማሪዎች ስለ ሰክሽን 504 አፈጻጸም ሂደት ይገልጻል። በድረ-ገጽ ላይ ቅጂዎች ይገኛሉ።

### ብቃት ያለው ማነው?

የአካል ስንክልና ያለባቸው ተማሪዎች አንድ ወይም ከዚያ በላይ ዋና ዋና ለህይወታቸው አስፈላጊ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን የሚገድብ የአካል ወይም የአእምሮ ስንኩልነት ካለባቸው ለመልሶ ማቋቋም በሰክሽን 504 መታቀፍ ይኖርባቸዋል። ሰክሽን 504 ስለ ዋና ዋና ለህይወታቸው አስፈላጊ እንቅስቃሴዎችን የሚገልጸው "ራስን ስለመንከባከብ፣ በሰው ጉልበት/በእጅ የሚሠሩ ሥራዎችን ለመሥራት፣ ለመራመድ፣ ለማየት፣ ለመስማት፣ ለመናገር፣ ለመተንፈስ፣ ለመማር፣ ለመሥራት፣ ለመቆም፣ እቃ ለማንሳት፣ ለማጎንበስ፣ ለማንበብ፣ ለማስተዋል/ለትኩረት፣ ለማሰብ፣ እና ለመገናኘት" የመሳሰሉ ተግባራትን ለማከናወን አለመቻል ነዉ። ተማሪው/ዋ ባለበ(ባ)ት ስንክልና ምክንያ ከአንድ በላይ ዋነኛ ለህይወት አስፈላጊ የሆኑ እንቅስቃሴዎች ላይ አንድምታ ሊኖርበ(ባ)ት ይችላል።

የአካል ስንክልና በምርመራ መገኘቱ/መታወቁ አንድን ተማሪ ወዲያውኑ ለሰክሽን 504 ብቁ ሊያደርገው/ሊያደርጋት አይችልም። መምህራን ወይም ወላጆች/ሞግዚቶች ተማሪው(ዋ) ለሰክሽን 504 ብቁ ይሆናል/ትሆናለች የሚል ስሜት ካደረባቸው፣ የሰክሽን 504 ቡድን በልጁ(በልጅቱ) ት/ቤት ስብሰባ እንዲያደርግና ጉዳዩን እንዲያጤን ለመጠየቅ ይችላሉ። ቡድኑ የሚያካትተው የት/ቤት ሠራተኞችን፣ ሌሎች ስፔሻሊስቶችን፣ ወላጆች/ሞግዚቶችን፣ እና አስፈላጊ ከሆነ ተማሪው(ዋ)ን ጭምር ነው። ቡድኑ ከበርካታ ምንጮች ያገኛቸውን መረጃዎች (ለምሳሌ፡- ሪፖርት ካርዶችን፣ የምርመራ ሠነዶችን፣ የሜዲካል ሪፖርቶችን፣ እና ሌሎች መረጃዎችን) ተማሪው(ዋ) ለሰክሽን 504 ብቃት እንዳለው/እንዳላት ለመወሰን ይገመግማል። በሰክሽን 504 የታቀፉ ሁሉም ተማሪዎች መገልገያ/አኮሞዴሽን አያስፈልጋቸውም ይሆናል። ተማሪው/ዋ በእኩልነት በትምህርት ፕሮግራሞች እና እንቅስቃሴዎች ላይ የመሳተፍ/የመማር እድል እንዲኖረው/እንዲኖራት ለማስቻል መጠቀሚያ መሣሪያዎች ያስፈልጉ(ጓ)ት እንደሆነ ለመወሰን ቡድኑ የተማሪው(ዋ)ን አሠራር/አፈጻጸም ስንክልና ከሌላቸው ጓደኞች/እኩዮች ጋር ማመዛዘን/ማስተያየት አለበት። ቡድኑ ከግምት ውስጥ ማስገባት ያለበት አንዳንድ ሁነቶች ስንክልና ከሌለባቸው እኩዮች ጋር ሲመዛዘን፣ ተማሪው(ዋ)

- የት/ቤትን ሥራ ለማከናወን በተከታታይ ብዙ ጊዜ ይፈጅበታል/ይፈጅባታል፣
- የት/ቤት ሥራ ለውጥ እንዲደረግለ(ላ)ት ሁልጊዜ ይፈልጋል/ትፈልጋለች፣
- ብዙውን ጊዜ የትምህርት መርሃ ግብር ተደራሽነትን የሚያደናቅፍ ባህሪ ያሳያል/ታሳያለች፣እና
- ራሱ(ሷ)ን ለመርዳት እገዛ ያስፈልገዋል/ያስፈልጋላታል።

### የሰክሽን 504 እቅድ ምንድነው?

ተማሪ(ዋ) ለሰክሽን 504 አስፈላጊ ነገሮች መመሪያዎችን የማሟላት ብቃት ካለው/ካላት፣ ተማሪው(ዋ) በት/ቤት የሚጠቀምበት/የምትጠቀምበት አስፈላጊ ነገሮች በሰክሽን 504 እቅድ ይዘጋጃል። እቅዱ የስንክልናውን ዓይነት/ሁኔታ በመግለጽ፣ በስንክልና ምክንያት የሚያስከትለው የህይወት እንቅስቃሴ ስንክልና፣ የተማሪው(ዋ)ን ፍላጎት ለማሳካት መሟላት ያለባቸውን አስፈላጊ ገሮች፣እና አስፈላጊዎቹን ነገሮች ለመተግበርና ለማሟላት ኃላፊነት ያለበ(ባ)ትን ሰው/ሰዎች በግልፅ ማስቀመጥ አለበት።

የሰክሽን 504 እቅድን ማዘጋጀት የት/ቤት ኃላፊነት ነው። ነገር ግን፣ ወላጆች/ሞግዚቶች የሰክሽን 504 የቡድኑ አካል ስለሆኑ እቁዱ በሚሠራበት ወቅት አብረው መሳተፍ አለባቸው። አስፈላጊ ሲሆን ተማሪው/ዋ መጨመር አለበ(ባ)ት። ከእርስዎ ተማሪ ጋር በቀጥታ ለሚሠሩ መምህራን ስለ ፕላን የሚያሳውቅና የሚያስተባብር/የምታስተባብር፣ በየዓመቱ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ግምገማ የሚያደርግ/የምታደርግ ኬዝ-ማናጀር ይመደባል/ትመደባለች። MCPS ለሰክሽን 504 እቅዶች የመገናኛ ብዙሃን በይነመረብ ይጠቀማል።

### የኔ የወላጅነት መብቶች ምንድናቸው?

ወላጆች/ሞግዚቶች የሚከተሉት መብቶች ይኖሯቸዋል፡-

- ተማሪያቸው በስንክልና ምክንያት ምንም አድልዎ ሳይደረግበ(ባ)ት ከህዝባዊ የትምህርት ፕሮግራሞች ላይ በመሳተፍ ተጠቃሚ ለመሆን መቻል።
- ተማሪያቸውን የሚመለከቱ የማንነት መለያ፣ግምገማ፣ እና/ወይም እንዲሟላለት/እንዲሟላላት የተባሉትን መጠቀሚያ ነገሮች እንዲያውቁት ማድረት/ማወቅ።
- ተማሪያቸው ተገቢ የሆነ የህዝብ ትምህርት በነፃ እንዲያገኝ/እንድታገኝ። ይህ የሚያካትተዉ በተቻለ መጠን ስንክልና ከሌላቸው ተማሪዎች ጋር በተገቢ ሁኔታ እኩል ትምህርት የማግኘት መብት ጭምር ነዉ።
- ተማሪያቸው ስንክልና ከሌላቸው ተማሪዎች እኩል በት/ቤት ፕሮግራሞች እና ከከሪኩለም ውጪ በት/ቤት የሚደገፉ እንቅስቃሴዎች ላይ የመሳተፍ እድል እንዲኖረው/እንዲኖራት።
- የተማሪያቸውን የትምህርት ሪኮርድ/መረጃዎችን የመመርመር እና ቅጂ የማግኘት።
- የማንነት መለያ፣ ግምገማ፣ እና የምደባ/ፕሮግራም ከተለያዩ ምንጮች በተገኙ መረጃዎች እና የተማሪው(ዋ)ን ፍላጎት ከሚያውቁ ሰዎች በተገኘ መረጃ መሠረት የተሰጠ ውሳኔ፣ ግምገማው ምን ማለት እንደሆነና ስለ ምደባ ያሉትን አማራጮች።
- ስለ ተማሪያቸው መለያ፣ ስለ ግምገማ፣ ወይም ምደባ/ፕሮግራም ውሳኔው ካላረካቸው ስለ ጉዳዩ ሌላ መፍትሔ የመሻት መብት አላቸው።

የ MCPS ቅሬታ አጣሪ እና ውሳኔ ሰጪ ክፍል, 850 Hungerford Drive, Room 208, Rockville, Maryland 20850, MCPS ሰክሽን 504 ላይ የሚከሰቱ ቅሬታዎችን የመቆጣጠር ሃላፊነት አለበት። ቤተሰብ/ሞግዚቶች ሰክሽን 504 ውሳኔዎች ይግባኝ ለማለት MCPS ሰክሽን 504 አስተባባሪን በስልክ ቁጥር 240-740-3230 ለማግኘት ይችላሉ። MCPS የበራሪ ጽሑፍ ቅጂ፣በሂደት ላይ ያለውን መረጃ በጥንቃቄ መጠበቅ፡- 1973 ሰክሽን 504 የመልሶ ማቋቋም ደንብ ስለ ሰክሽን 504 የበለጠ ዝርዝር መረጃ ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል።

## ስለ ሰክሽን 504 የበለጠ ለማወቅ የምችለው ከየት ነው?

ስለ ሰክሽን 504 ምክረሃሳቦችን/accommodations እና በርካታ መረጃዎችን ከሚከተሉት ምንጮች ለማግኘት ይችላሉ።

| በት/ቤት ከሚገኝ የሰክሽን 504 አስተባባሪ | |
|---|---|
| MCPS የሰክሽን 504 አስተባባሪ | 240-740-3230 |
| MCPS የስነ ስርአት ማስከበር እና ውሳኔ ሰጭ ዩኒት/Resolution and Compliance Unit<br>www.montgomeryschoolsmd.org/departments/special-education/compliance/section-504.aspx | 240-740-3230 |
| U.S. Department of Education Office for Civil Rights<br>ዩ.ኤስ. የትምህርት ዲፓርትመንት የዜጎች መብቶች ጽ/ቤት<br>http://wdcrobcolp01.ed.gov/CFAPPS/OCR/contactus.cfm | 215-656-8541<br>1-800-421-3481 |

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማን ነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸ ውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመ ንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትም ህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞን ትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ፡- ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረ ግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

<table>
<tr><td>MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</td><td>MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</td></tr>
<tr><td>Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org</td><td>Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td>በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ</td><td>በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ</td></tr>
<tr><td>Section 504 Coordinator<br>Office of Academic Officer<br>Resolution and Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 208, Rockville, MD 20850<br>240-740-3230<br>RACU@mcpsmd.org</td><td>ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td colspan="2">"Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች</td></tr>
<tr><td colspan="2">Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org</td></tr>
</table>

**ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፦ U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳለጠ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፦ 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኤሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

Maryland's Largest School District

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

ህትመት፡- Department of Materials Management
for the Resolution and Compliance Unit
0651.23ct • Editorial, Graphics & Publishing Services • 12/22 • NP